# ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ታክሲዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ ለማድረግ የወጣው መመሪያ ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 898/2014

1. **አውጪው ባለስልጣን**

   የገንዘብ ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ( እንደተሻሻለ ) አንቀጽ 129(1) በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ታክሲዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ስለሚሆኑበት ሁኔታ የወጣው መመሪያ ቁጥር 70/2013 ዓ.ም ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 898/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ማሻሻያ**

   ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ታክሲዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ስለሚሆኑበት ሁኔታ የወጣው መመሪያ ቁጥር 70/2013 ዓ.ም አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ተተክቷል፡፡

   “10 (2) የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር፡-

   ሀ) ጥያቄው በሥራ ላይ ያሉ ታክሲዎችን በአዲስ ለመተካት ከሆነ የታክሲ አገልግሎት ሰጪ ማህበሩን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም የታደሰ የንግድ ፈቃድ እና ያገለገለውን ተሽከርካሪ የሠሌዳ ቁጥር እንዲሁም ቀረጥና ታክስ የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጠውን ማስረጃ ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ለገንዘብ ሚኒስቴር ይልካል፣

   ለ) ጥያቄው የቀረበው በአዲስ የተሽከርካሪ አገልግሎት ሰጪ ማህበራት እና/ወይም አዲስ ተሽከርካሪ ለመግዛት ከሆነ የታክሲ አገልግሎት ሰጪ ማህበሩን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ማስረጃዎችን ለገንዘብ ሚኒስቴር ይልካል፣"

4. **ማሻሻያው የሚፀናበት ቀን**

   ይህ ማሻሻያ ከሰኔ 9 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ሰኔ 09 ቀን 2014 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*